*የቅንጅት አመራሮችን ከእስር በማስፈታት ኺደት የተሳተፈው የሽምግልና ቡድን፣ የኃይማኖት አባቶችንም እርስ በርሳቸውና ኦነግን ከመንግሥት ጋር ለማደራደር፤ ከኦነግ ጋር በተያያዘ በቁጥር ስር የዋሉ እስረኞችን ለማስፈታት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በሌላ በኩል ኦነግን ከመንግሥት ጋር ለማደራደር ሦስት አባላት ያሉት ሌላ ቡድንም ተቋቁሟል። እነዚህ የሽምግልና ቡድኖች በሀገራዊው ተጽዕኖ ላይ ምን ዓይነት የፖለቲካ ድባብ ያሳድራሉ? ስትል የእንቢልታ ጋዜጣ ዘጋቢ ጽዮን ግርማ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የተለያዩ ሰዎች ትጠይቃለች።*

# የፖለቲካ ውዝግቡና የሽማግሌዎቹ ሚና

"... አዲስ ዓመት በመጣ ቁጥር እስረኞችን የማስፈታት ባህል በኢትዮጵያ ስላለ ደርግ ከሥልጣን ወርዶ የሽግግር መንግሥት ሲቋቋም፤ እስረኞች ቢፈቱ የኢትዮጵያ መንግሥትን እንደሚያስመሠግነው በመግለጽ በ1984 ዓ.ም. ደብዳቤ ጽፈናል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ለመንግሥት የዘመን መለወጫ ሠላምታ ስንጽፍ፣ እስረኞች ምሕረት ተደርጎላቸው ቢፈቱ ለመንግሥት ከበሬታ ያስገኛል፣ እያልን ሳናሳስብ ያለፍንበት ጊዜ የለም። በ1990 ዓ.ም. የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ሲጀመር ግን ትኩረታችንን ወደዛው በማድረጋችንና ለመከታተል ባለመቻላችን ተቋርጦ ቆየ። በ1997 ዓ.ም. በተደረገው ሀገራዊ ምርጫ ግን በመንግሥትና በተቃዋሚዎች መካከል አለመግባባትና አለመተማመን በመፈጠሩ ያንን ተከትሎ ፓርላማ አንገባም በማለታቸው እኛም እኛና ሌሎች ሰዎች ያገኛችሁትን ድምፅ ይዛችሁ ብትገቡ ይሻላል የሚል ምክር መስጠት ጀመርን። የሽምግልና ኮሚቴው ጥንስስም የተጀመረው ፓርላማ ግቡ አትግቡ በሚል ከተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር በተያያዘ ሲደረግ በነበረው የተናጠልና የቡድን ውይይት ነው" በማለት ፕሮፌሠር ኤፍሬም ይስኃቅ የሽምግልና ኮሚቴውን አጀማመር አስመልክተው በ1999 ዓ.ም. ማጠናቀቂያ ላይ የገለጹት ይታወሳል።

ፕሮፌሠር ኤፍሬም ይስኃቅ የሀገር ሽማግሌዎች ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው። እንደሳቸው አባባል ይህ ኮሚቴ የተቋቋመው፣ በወቅቱ በሀገሪቱ ላይ ተወጣጥሎ የነበረውን የፖለቲካ አለት አብርዶ ሠላም ማምጣት ነው። ከሽማግሌዎች ኮሚቴ ጥንስስ በኋላም በመንግሥትና በፓርላማ የቅንጅት አመራሮች መካከል፣ መግባባትና ፍቅር እንዲፈጠር ለሦስት ወራት ጥረት ቢያደርጉም፣ ከመቀዝቀዝ ይልቅ እየተጋጋለ መጥቶ ኹኔታው ወደ ግጭት ሲሸጋገር፣ የሰው ሕይወትና ንብረት ጠፍቶ፣ የፓርቲው መሪዎች እስር ቤት ሲገቡ፣ ኮሚቴው ተጠናክሮ እንቅስቃሴውን ቀጥሎ እንደነበር ይገልፃሉ።

ሐምሌ 13 ቀን 1999 ዓ.ም.፣ የቅንጅት አመራሮች ከእስር ሲፈቱ፣ የሽምግልና ኮሚቴው ወደ 23 የሚጠጉ የሽምግልና ቡድን ይዞ በሒልተን ሆቴል መግለጫ ሰጠ። ይህ ኮሚቴም በቀጣይ ሌሎች የማሸማገል ሥራዎችን መሥራት ቀጠለ።

# የኮሚቴው ስብስብ

ስማቸውን መግለጽ ያልፈለጉ አንድ አባል፣ የኮሚቴውን አደረጃጀት በአራት ምድብ ይከፍሉታል። በኮሚቴው ውስጥ ከልባቸውና ለእውነት ለሀገር ሠላም፣ አንድነትና እርቅ ቆርጠውና ፈልገው የተነሱት በአንደኛ ምድብ ውስጥ ያስቀምጧቸዋል። ሁለተኛዎቹ:- በቋሚነት የሚሠሩት ሥራ የሌላቸው ሲሆኑ፣ መሠረታዊ የኾነና ጠቃሚ ሃሳብ በማመንጨት ባይሳተፉም ዕድሚያቸው የገፉ በመኾናቸው ብቻ የተካተቱ ናቸው ይሏቸዋል። ሦስተኛዎቹ:- "ግርግር ለሌባ ይመቻል" እንደሚባለው በመንግሥት በኩል ተቀባይነት እና እውቂያ እንዲያገኙ በማጎብደድ፣ ታዋቂነትን ለማትረፍና የተለያዩ ጥቅሞችን ለማግኘት የገቡ ናቸው። አራተኛዎቹ:- በተለያየ ምክንያት መጀመሪያውኑ ታዋቂነትን ያተረፉ፣ የገንዘብ ጥቅም የማይፈልጉ ኾነው፣ ነገር ግን መንግሥትን ተጭነው ማስከፋት ሳይፈልጉ፣ ከላይ ከላይ ባላቸው ዝና ላይ ዝናን ለመጨመር የሚፈልጉ ናቸው በሚል ይከፍሏቸዋል።

"ፕሮፌሠር ኤፍሬም የሚመሩት 'ፒስ ኤንድ ዴቨሎፕመንት' እና ፓስተር ዳንኤል ገ/ሥላሴ የሚመሩት 'ፕሪዝን ፌሎሽፕ' የሽምግልና ኮሚቴው አባል ድርጅቶች ናቸው። ሌሎች ማኅበራትና ድርጅቶች የኮሚቴው አባል ሲሆኑ፣ አብዛኞቹ አባላት በግል የተቀላቀሉ ናቸው።

“ፕሮፌሠር ኤፍሬም፤ በሀገር ውስጥ ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጀምሮ በርካታ የመንግሥት ባለሥልጣናትን በማግኘት ማነጋገር የሚችሉበት ድልድይ፤ ፓስተር ዳንኤል ደግሞ በድርጅታቸው አማካኝነት ባላቸው ሠንሰለት ለሽምግልናው ሂደት አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስችል ገንዘብ የማግኘት አቅም አላቸው። ስለዚህም በተለያየ ምክንያት ከተሰበሰቡ በርካታ ሽማግሌዎች ውስጥ ሁለቱ፣ የኮሚቴው ሞተር እንደሆኑ እኚህ ስማቸውን መግለፅ ያልፈለጉ አባል ይናገራሉ።

የቅንጅት አመራሮችን ለማስፈታት በተደረገው ጥረትም፣ በመጨረሻው ቀን የተሰባሰቡት “በርካቶች” ምንም ሚና አልነበራቸውም ይላሉ። በሁለቱ ሰዎች ላይ አትሌት ኃይሌ ገ/ሥላሴን ጨምሮ ለ18 ወራት ድርድሩ ከዘለቀ በኋላ በመጨረሻ እስረኞቹ ፕሮፌሠር ኤፍሬምን ላደረጉት ጥረት አመሥግነው፤ ነገር ግን ከዚያች ዕለት ጀምሮ ሊያገኟቸውና ሊያነጋግሯቸው እንደማይችሉ፣ እንደማይፈልጉም ሲገልፁላቸው፤ የኢትዮጵያ ጠበቆች ማኅበር ፕሬዝዳንትና በፌደራል ፍርድ ቤቶች የሕግ አማካሪና ጠበቃ የሆኑትን አቶ ታምሩ ወንድም አገኘሁን ይዘው በድጋሚ መሄዳቸውን፣ ጉዳዩም እልባት እስኪያገኝ ሁለቱንም ወገን ሲያነጋግሩ የነበሩት እነዚህ ሰዎች ብቻ እንደነበሩ እኚሁ አባል ይገልፃሉ።

በቀጣይም በተደረጉ ሌሎች ሂደቶች፣ በጉዳዩ ላይ በአንድ እጅ ጣት ከሚቆጠሩ ሰዎች በላይ፣ ተሳትፎ እንዳልነበራቸውም ይገልፃሉ። ሌሎቹም በሽምግልናው ኮሚቴ በሚደረጉ በማናቸውም ሂደቶች ላይ ጠቃሚ የሚባሉ ሃሳቦችን እንኳን ሲሰነዝሩ እንደማይታዩ ይገልፃሉ።

## የቅንጅት አመራሮችንና ሌሎች ተከሳሾችን በማስፈታት የሽማግሌዎች ሚና

ፕሮፌሠር ኤፍሬም ይስኃቅ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን አነጋግረው ይሁንታ ካገኙ በኋላ፤ ወደ እስረኞቹ በመሄድ እነርሱንም ማነጋገር ጀመሩ። በወቅቱ እሳቸው እንደተናገሩትም ለዚሁ ጉዳይ ብለው ከሚኖሩበት አሜሪካን ሀገር ለ11 ጊዜያት ተመላልሰዋል። በቆይታቸውም በተደጋጋሚ ሁለቱንም ወገን ለማነጋገር ጥረት አድርገዋል።

“… ፕሮፌሠር ኤፍሬምና እስረኞቹን አላግባባ ያለው ጉዳይ፣ ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ እንዲፈርሙ የተላከው ሠነድ ነበር። እስረኞቹ (ሁሉም ባይሆኑ) ያንን ሠነድ የመፈረም ፍላጎት አልነበራቸውም። በተለያየ ጊዜ ቃላቶቹ እየተለዋወጡና እየተቀያየሩ ቢመጡም፣ ለመፈረም ፈቃደኛ የሚሆን አልተገኘም። ፕሮፌሠሩም ሰነዱን የማስለወጥ ወይም የማስቀየር ሥልጣን ስላልነበራቸው እስረኞቹ እግር ላይ እየወደቁና እየለመኑ ለማሳመን ጥረት ያደርጉ ነበር። የሕግ ባለሞያው አቶ ታምሩ ወንድምአገኘሁ እስከገቡበት የመጨረሻው ወራት ድረስም የፕሮፌሠሩ አካሄድ የተሳካ የሽምግልና አካሄድ አልነበረም ይላሉ” ሌላ ስማቸውን መግለጽ ያልፈለጉ በሂደቱ ውስጥ የነበሩ አባል።

በቅንጅት አመራርነታቸው በእስር ላይ የነበሩትና በዚህ የሽምግልና ሂደት ከእስር የተፈቱት የአሁኑ የአንድነት ፓርቲ ም/ሊቀመንበርና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ዶ/ር ኃይሉ አርኣያ፤ “… የነበረው የሽምግልና ሚና የልመና ነው ማለት ይቻላል። ከፕሮፌሠር ኤፍሬም ጋር እንነጋገራለን እንስማማለን፤ ከዚያም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ሄደው እስር ቤት ያሉት ተስማምተዋል ክብደት ይስጡት ብለው ይናገራሉ። ተመልሰው እኛ ጋር ይመጡና ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲህ ብለውኛል ምን ማድረግ ይቻላል ብለው እኛን ያማክሩናል። በመጨረሻ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍላጎት ተከናውኗል የጠየቁትን በማሟላት ከእስር ወጥተናል። በመሆኑም የሽምግልናው ሚና ከመካከል ኾኖ የማመላለስ እንጂ ድካማቸው ተጽዕኖ አልነበረውም፤ በማጠናቀቂያው የታየውም የሽምግልና ውጤት ሳይሆን የልመና ውጤት ነው። በሽምግልናው ሂደት ቃል የተገቡ ነገሮችም ተፈፃሚ አልሆኑም” ይላሉ።

የግንቦት 7 ንቅናቄን መሥርተው በአሜሪካን ሀገር የሚገኙት፣ የቅንጅቱ የቀድሞ አመራር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከእስር ከተፈቱ በኋላ የሀገር ሽማግሌዎቹን ክፉኛ ይወቅሳሉ፤ ሌሎች የቅንጅቱ አመራር የነበሩና በዚህ ሂደት ከእስር የተፈቱትም “የተገባልን ቃል ተፈፃሚ አልሆነም” ሲሉ ይኮንናሉ።

የቀድሞው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ፕሬዝዳንት ዶ/ር ነጋሶ በበኩላቸው፤ የቅንጅት አመራሮችና ሌሎች እስረኞች ከእስር እንዲፈቱ የተካሄደው ሽምግልና ሂደትና የተጠናቀቀበትን ሁኔታ፤ ከጅምሩ ይዳስሳሉ። ከምርጫው በኋላ በግንቦት 7 ቀን ማምሻውን ጠ/ሚኒስትሩ “አሸንፈናል” ብለው

ከገለፁ በኋላ፣ በተለያዩ ሁኔታዎች ጊዜያዊ የሚመስል ዓዋጅ ዓውጀው፣ ሠራዊት አሠማርተው፣ በአንቀፅ 30 በሕገመንግሥቱ የተፈቀደውን መብት እንዲከለከል አድርገው የታፈነ ሁኔታ በመፍጠራቸው፣ ሕገመንግሥቱን ያልተከተለ ጊዜያዊ ዓዋጅ በማወጃቸው አመፅ ተነሳስቶ ከ200 ሰዎች በላይ ተገደሉ፣ በርካቶች ቆሰሉ፣ የቅንጅትን አመራሮች ጨምሮ በርካቶች ታሰሩ። እነዚህን እስረኞች ለማስፈታት የተደረገው ሽምግልና የችግሩ አካል የሆኑትን ሁለት ሰዎች በእኩል በማየት ተደረገ ሳይሆን፤ እስረኞቹን የኢህአዴግን ቅድመ ሁኔታዎች እንዲቀበሉ በማድረግ፣ ይህን የማትቀበሉ ከሆነ የክስ ሂደታችሁ በዚህ መንገድ ይጠናቀቃል በሚል በማስፈራራትና ፍትሐዊ ባልሆነ መንገድ የተከናወነ ሽምግልና እንደሆነ ይገልፃሉ።

የሽምግልናው ሂደት ፍትሐዊ እና ለአንድ ወገን ያጋደለ ባይሆን ኖሮ በኢህአዴግ የተፈፀሙት የግድያና የማቁሰል ወንጀሎች በሽማግሌዎቹ ሊታይ በተገባ ነበር ይላሉ ዶ/ር ነጋሶ።

የሽምግልና ቡድኑን እንዴት እንደተቀላቀሉ በመግለፅ፣ አስተያየታቸውን መስጠት የሚጀምሩት የኢትዮጵያ ጠበቆች ማኅበር ፕሬዝዳንትና የሕግ ባለሙያው አቶ ታምሩ ወንድምአገኘሁ ናቸው።

"የቅንጅት አመራሮችና ሌሎች ከነሱ ጋርም የተያዙ ሰዎች፣ ከምርጫ 97 በኋላ በተከሰቱ ችግሮች ምክንያት እስር ቤት ስለነበሩና ክስ ቀርቦባቸው ስለነበረ፤ በእነዚሁ ሰዎች መታሰር ምክንያት ከዚህ በፊት እንደ ሕግ ባለሞያነቴ ከሌሎች መሠል ጓደኞቼ ጋር ሆነን በመጀመሪያ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ፣ ከዚያም ሕገ መንግሥታዊ የዋስትና መብታቸውና ሌሎች ነገሮች እንዲሟሉላቸው ጥያቄ አቅርበንና ተከራክረን ነበር። በኋላ ያቀረብነው ጥያቄ ውድቅ ተደረገ። እኛም ከመከላከሉ ሂደት ወጥተን ሳለ፤ ቀደም ሲል ለ18 ወራት ይሄን ነገር ሲከታተሉ በቆዩት ፕሮፌሠር ኤፍሬም ጠያቂነት ጉዳዩ ጫፍ ከደረሰ በኋላ በሚያዝያ 29 ቀን 1999 ዓ.ም. ተቀላቀልኩ።

"ፕሮፌሠር ኤፍሬም እንደነገሩኝ ነገሩ በሙሉ ተበላሽቶ ውሉን ስቷል። ይኸውም እስረኞቹ ፕሮፌሠር ኤፍሬምን ጠርተው "እስከዛሬ ድረስ ስላደረጉልን እናመሠግናለን፤ ከእንግዲህ ወዲህ አትምጡብን፤ በሃሳቦት አንስማማም፣ የቀረበውን ሃሳብ በፍፁም አንቀበልምና እንዳይመጡብን" ብለው አሰናብተውኛል። እስረኞቹና ጠ/ሚሩ የተለያዩባቸው ነጥቦች እነዚህ ናቸውና ይኼንን አይተህ አንተ ልትረዳኝ የምትችለው ነገር ካለ እባክህ ሃሳብህን ስጠኝ ብለው ጠየቁኝ። እኔም ነገሮችን አየሁና ልረዳቸው የምችለው ነገር እንዳለ ጠቁሜያቸው፣ በመጨረሻ የተዘጋው በር ተከፍቶ እስረኞቹ ሊፈቱ ችለዋል" ብለውናል።

ሽምግልና ሲባል በብዙ መልክ ሊታይ የሚችል ነው። አንዱ የግልግል ዳኝነት የሚባለው ዓይነት ነው። የሽምግልናው ሂደት በዚህ መልክ ታይቶ ከሆነ ስህተት ነው። ሽማግሌ ነን ብለው እዛ ጉዳይ ውስጥ የገቡት፤ ሁለቱ ያልተግባቡ ወገኖች ማለትም መንግሥትም የታሰሩት የፖለቲካ ፓርቲ አባላትም መርጠዋቸው ወይም ጠይቀዋቸው የገቡ አይደሉም። እነዚህ በሽምግልና የተሰማሩ ሰዎች የሥልጣን ገደብ (Term of Reference) አልተሰጣቸውም። በተጨማሪም ደግሞ ሁለቱ ተፋላሚ ወገኖች በአንድ መድረክ የሚቆሙ እኩያሞች አይደሉም ማለት ይቻላል። "መንግሥት" ሉዓላዊ ሥልጣን ያለው አካል ነው። እስረኞቹ ደግሞ ተከሰው ነፃነታቸውን አጥተው እስር ቤት ያሉ ወገኖች ናቸው። በዚህ ሁኔታ ሽማግሌ ሆነው የገቡ ሰዎች በማንም ያልተወከሉ በመሆናቸው ፈፅሞ ሥልጣን የሌላቸው፣ ያገር ጉዳይ ያገባናል፣ የሕግ መጣስ፣ መደፈር ጉዳይ ይመለከተናል፤ በሀገራችን ሠላም ሊኖር ይገባል። ያለው ሁኔታ ወደ አልሆነ አቅጣጫ እያመራ ነው። ስለዚህ ባለቤቶች ነን በሚል በራሳቸው ስሜት እዚህ ጉዳይ ውስጥ የገቡ ናቸው።

ሥልጣን የሌላቸው ናቸው። ሥልጣን ስለሌላቸውም በሚል የሁለቱንም ወገን አዳምጦና አይቶ፣ የሁለቱም ክርክር በተነፃፃሪነት አንድ መድረክ ላይ አስቀምጦ "ይሄኛው በዚህ ልክ ነው።"፤ "ይኼኛው በዚህ ጥፋት ነው" ብሎ የመወሰን ሥልጣን ስለሌላቸው፤ የነሱ ሥልጣን ከሁለቱም ሰምቶ ቢቻል ሁለቱንም አንዳንድ የከረረ አቋማቸውን እንዲያለዝቡ በማግባባት ወይም በመለመን አማራጭ ሃሳቦችን ለራሳቸው በማቅረብ፣ እራሳቸው እንዲወስኑ ማግባባት ነው የሽማግሌዎቹ ድርሻ። ስለዚህ ውሳኔውን የሚወስኑት ሽማግሌዎቹ ሳይሆኑ በእዚህ ግራ ቀኝ የቆሙ አካላት ናቸው። በዚህም የተነሳ እኔ በግሌ ያን ውሳኔ የወሰኑት ሽማግሌዎቹ ሳይሆኑ፣ "የቀረበው ሁኔታ በዚህ ደረጃ ይመቸናል፤ ከዚህ ከፍ ማለት አይቻልም፤ በመጨረሻ የተሰጠው ይሄ ነው ስለዚህ ባለው ሁኔታ ይሄንን መቀበል ይሻላል" የሚለውን የመጨረሻ ውሳኔ

የተቀበሉትና የወሰኑት ሁለቱ ወገኖች ናቸው ሽምግልናቸው የዕድሜ ሊሆን ይችላል፣ የሥልጣን ግን አይደለም። በዚህም የተነሳ ከሽማግሌዎቹ በድለውናል የሚለው ጥያቄ ሊነሳም፣ ሊኖርም አይችልም ይላሉ አቶ ታምሩ።

በሽምግልናው ሂደት የነበሩ ስማቸውን መግለፅ ያልፈለጉ ሌላ አባል፣ ቃል ተገብቶ አልተፈፀመም በሚል በተደጋጋሚ ስለሚነሳው ወቀሳ ሲገልፁ፤ ተገባ ከተባለው ቃል አንደኛው በቅንጅት ስም የታሰሩ እስረኞች በሙሉ እንዲለቀቁ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መስማማታቸው ተገልፆላቸው ነበር፤ ነገር ግን በቅንጅት ስም የታሰሩ እስረኞች፤ እነማን እንደሆኑ እና የት እንደታሰሩ የሚገልጽ መረጃ በማሰባሰብ ወይም እስረኞች ሊከታተሉት በሚችሉት የመንግሥት ሚዲያና እንደጀርመንና ቪኦኤ ባሉ ራዲዮኖች አስነግሮ ስማቸውንና የሚገኙበትን እስር ቤት ለሽማግሌዎቹ ኮሚቴ መረጃ መስጠት ይገባ ነበር። ነገር ግን አመራሮቹ ከእስር እንደተፈቱ አንድ ወኪል እንኳን ሳያስቀምጡ ተጠራርገው ወደ ውጭ በመሄድ አተካሮ ነው የገጠሙት፤ በመጨረሻም የተፈቱት ከውጭ ከተመለሱም በኋላ ቢሆን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ አሰባስበው ካመጧቸው የጥቂት እስረኞች ስም ዝርዝር ውጪ የቀረበ ነገር የለም። እነሱ ደግሞ ተፈተዋል ብለውናል።

ሌላው ከእስር ከተለቀቁ በኋላ እና ከመታሰራቸው በፊት ባስቀመጧቸው ስምንት ነጥቦች ዙሪያ ከመንግሥት ጋር መወያየት የሚል የነበረ ሲሆን፤ እሱንም ቢሆን ስማቸውና ምልክታቸውን ሌላው ቡድን ወስዶት፣ ከእስር የተፈቱትም ሦስት ቦታ ተከፋፍለው ባሉበት ሁኔታ ከማን ጋር ውይይት ሊደረግ ይችላል? በዚህ ጉዳይ "የተገባልን አልተፈፀመም" ከማለት ውጪ ሽማግሌዎቹን ቀርቦ ያነጋገረም እንዳልነበረ ይገልፃሉ።

## ሽምግልናው በቤተክህነት

የሽምግልና ኮሚቴው ስብስብ እስካሁን እንደቀጠለ የሚናገሩት አቶ ታምሩ፤የቅንጅት አመራሮች ከተፈቱ በኋላ በቤተክህነት ውስጥ ተፈጥሯል የተባለውን መከፋፈል መሠረት በማድረግ ሌላ እርቅ ተጀምሮ እንደነበር ይገልፃሉ።

የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ብዙ የሚነጣጠል ባለመሆኑና ለ፤ ሺህ 600 ዓመታት ሳትነጣጠል የኖረችው ቤተክህነት፣ ኢትዮጵያ ያሉና አሜሪካ ያሉ በሚል፤ ከዚያም አልፎ ጳጳሳት በውጭ እስከመሾም ያደረሰ ጉዳይ በሠላም መፈታት አለበት የሚል አቋም በሽምግልና ስብስቡ አባላት ውስጥ ስለነበር መግባባት እንዲኖር ከፍተኛ ጥረት መደረጉን አቶ ታምሩ ይገልፃሉ።

## ኦነግና- የሽምግልና ቡድን

እ.ኤ.አ. በ2004 ዓ.ም. የትጥቅ ትግል የሚያካሂደው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) መቋዲሾ ላይ ለሁለት ይሰነጠቃል። አቶ ገለሳ ዲልቦ፣ አቶ ኢብሳ ጉተማ እና አቶ ዐብዩ ገለታ የተከፈለው ቡድን "ኦነግ ነን" ብለው መጠየቅ ቢጀምሩም በአቶ ዳውድ ኢብሳ የሚመራው የኦነግ ቡድን አመራሩን ይዞ ይቀጥላል።

በሐምሌ ወር 2000 ዓ.ም. ደግሞ፣ ጉዳያቸውንም ፍርድ ቤት ወስደው መከራከር ይጀምራሉ። ኦነግ ሌላ የመሰንጠቅ አደጋ ገጠመው። በአቶ ዳውድ ኢብሳ የሚመራው ቡድን እና በዶ/ር ሌንጮ ባቲ የሚመራው ሌላ ቡድን። ከዚህ ክፍፍል ውጭ ደግሞ አስቀድመው ከኦነግ አባልነታቸው የለቀቁ አቶ ሌንጮ ለታና አባቢያ አባጀቢር ያሉበት ሌላ ቡድን ተፈጥሯል።

በመጀመሪያው ክፍፍል ወቅት የተገነጠሉት የእነ ገለሳ ዲልቦ ቡድን የት እንዳለ ባለመታወቁ፤ በዋናነት የሚታወቁ ሦስት ቡድኖች አሉ፤ ቡድን አንድ፡- መቀመጫውን አስመራ ውስጥ ያደረገው በአቶ ዳውድ ኢብሳ የሚመራው፤ ቡድን ሁለት፡- መቀመጫውን በአሜሪካን ሀገር ያደረገው በዶ/ር ሌንጮ ባቲና በአቶ ሐሰን ሁሴን የሚመራው፤ ቡድን ሦስት፡- ቀድሞውኑ ከኦነግ የወጣና አቶ ሌንጮ ለታ፣ አባቢያ አባጀቢር፤ አቶ ዲማ ነገዎ እና ኩለኒ ጉዲና ያሉበት ቡድን ነው።

## ሽምግልናው ከየትኛው ቡድን ጋር

ኦነግንና ኢህአዴግን ለማሸማገል ግንባር ቀደሙና የመጀመሪያው አሸማጋይ ኢሳያስ አፈወርቂ እንደነበሩ የሚገልጹት ዶ/ር ነጋሶ ሽምግልናው ሳይሳካ መጠናቀቁን ይናገራሉ።

በድጋሚ 1997 ዓ.ም. ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከቢቢሲ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከኦነግ ጋር እንደሚደራደሩ በመግለፃቸው፤ የጀርመን ፕሬዝዳንት የአፍሪካ መንግሥታትና የጀርመን መንግሥት የጋራ ትብብር እንዴት መሆን አለበት፣ በሚለው ላይ ለመወያየት የአፍሪካ መሪዎችን “ቦን” ከተማ ላይ ሲጠሩ፤ አቶ ሌንጮ ለታ የኦነግ አገናኝ ሆነው ወደ ቦን አመሩ። ነገር ግን ጠ/ሚኒስትሩ፤ የኦነግ አመራሮች ሕገመንግሥቱን ከተቀበሉ፣ በሠላማዊ መንገድ ለመታገል ፍቃደኛ ከሆኑና መሣሪያ ካስቀመጡ ብቻ ለመወያየት እንደሚችሉ በመግለፃቸው የኦነግ አመራር ሁኔታውን ለመቀበል ፍቃደኛ ባለመሆኑ ድርድሩ ሳይሳካ መቅረቱን ዶ/ር ነጋሶ ይገልፃሉ።

ተጀመረ የተባለውን የሽምግልና ሂደት ጠንቅቀው የሚያውቁ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ሲገልፁ፤ በፕሮፌሠር ኤፍሬም ይስኃቅ የሚመራው የሽምግልና ቡድን፣ ከኢትዮጵያ ውጪ በትጥቅ ትግል ላይ የሚገኘው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ከመንግሥት ጋር ተደራድሮና መሣሪያውን ጥሎ፣ ሀገር ውስጥ ገብቶ በሠላማዊ መንገድ ትግል እንዲያደርግ ለማስቻል እንቅስቃሴ ይጀምራል።

ሀገር ውስጥ ያሉትንና ውጭ ሀገር የሚገኙትን የሀገር ሽማግሌዎች ጨምሮ፣ በጥቅምት ወይም በኅዳር ወር 2001 ዓ.ም. አዲስ አበባ ላይ የሠላም ኮንፈረንስ ለማካሄድ፤ አቶ ዲማ ነገዎ፣ ወ/ሮ ኩለኒ ጉደታ፣ አቶ ሌንጮ ለታ እና አባቢያ አባጆቢር ሥራ አስፈፃሚ ሆነው እንቅስቃሴ ይጀምራሉ።

ፕሮፌሠር ኤፍሬም ይስኃቅ፤ ለዚህ የሠላም ኮንፍረንስ ሀገር ውስጥ ገብተው መሣተፍ እንዲችሉ ለማስፈቀድ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ተፍ ተፍ ሲሉ ቆይተውና፣ አባቢያ ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ባሉበት ሰዓት ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ፕሮፌሠር ኤፍሬም ይስኃቅ ወደ አሜሪካን ሀገር ተመልሰው ሲሄዱ ለሠላም ኮንፈረንሱ የሚደረገው እንቅስቃሴም ለጊዜው ይቋረጣል።

## ሁለተኛው የሽምግልና ቡድን

በአዲስ አበባ ዙሪያ፣ ከሐረር እስከ ወለጋ፣ ከከሚሴ እስከ ቦረና ያሉ እስከ 130 የሚሆኑ የኦሮሞ ሽማግሌዎችን በኢምፔሪያል ሆቴል የሰብሰበው ሦስት አባላት ያሉት ሁለተኛው የሽማግሌዎች ቡድን፤ ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ ኦነግና መንግሥት ተገናኝተውና ተቀራርበው እንዲነጋገሩ ለማድረግ ጥረት መጀመራቸውን ከኦነጉ መሪ ከአቶ ዳውድ ኢብሳ ጋር ባደረጉት ውይይት፣ የህዝቡን ድምፅ ሰምተው ያለምንም መዘግየት ወደ ድርድር የሚመጡበት ሁኔታ እንደሚያመቻቹ ፍቃደኝነታቸውን እንዳሳዩዋቸው በመግለጽ፤ ስብሰባው የደረሰበትን የውሳኔ ሃሳብ የሚያዘጋጅ 30 አባላት ያሉት ኮሚቴ አቋቁመው፣ የተዘጋጀውን የውሳኔ ሃሳብ ለኦነግና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደሚያቀርቡ ቃል ገብተው ስብሰባውን በትነዋል።

ይህ ሦስት አባላት ያሉት ቡድን፤ የመካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ፕሬዝዳንት ቄስ ኢተፋ ጎበና፣ በደርግ ጊዜ ለ10 ዓመታት በኦነግነት ተጠርጥረው በእስር ላይ የነበሩ፣ ኦነግ አዲስ አበባ በነበረበት ጊዜ የአቶ ሌንጮ ለታ ረዳት የነበሩትና አሁን በአክስፋም ተቀጥረው የሚሠሩት፣ የኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ መሥራች የሆኑት አቶ አበራ ቶላ፤ እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት የታላላቅ ኃይቆች ልዑክ አምባሣደር ብርሃኑ ዲንቃ ይገኙበታል።

ባለፈው ማክሰኞም አምባሣደር ብርሃኑ ዲንቃን ጠቅሶ ሱዳን ትሪቡን እንደዘገበው የኢትዮጵያ መንግሥት ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ጋር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለመነጋገር ዝግጁ መሆኑን እንዳረጋገጠላቸው መግለፃቸውን ነው።

ቡድኑ ከሦስት የኦሮሞ ጎሣዎች የተውጣጡ የሀገር ሽማግሌዎች፤ ከዳውድ ኢብሳና ከተማም ዩሱፍ ጋር በአምስተርዳም ባደረጉት ውይይት፤ ሕገመንግሥቱን አክብረው ለመንቀሳቀስ ዝግጁ መሆናቸውን በፊርማ እንዳረጋገጡላቸው ገልፀዋል።

ጠ/ሚ መለስ ዜናዊም፤ በተናጠል ጠርተው መንግሥታቸው ከኦነግ ጋር ለመነጋገር ዝግጁ እንደሆነ እንደገለፁላቸው መናገራቸው ተዘግቧል።

"እኛ ቡድኖች አይደለንም፤ ሦስት ሰዎች ነን" ሲሉ ለእንቢልታ ጋዜጣ የገለፁት አምባሣደር ብርሃኑ ዲንቃ፤ "ጉዳዩ በሽምግልና እንዲታይ ለማድረግ ጥረት የጀመርነው ሦስታችንም ከዚህ በፊት ተያይተን አናውቅም። የሀገር ሽማግሌዎች በተናጠል መርጠው በመንግሥትና በኦነግ መካከል እርቅ እንድናመጣ ያዘዙን ነን" ብለዋል።

የሀገር ሽማግሌዎቹ በላኳቸው መሠረት፤ ከኦነግና ከመንግሥት ተቀባይነት እንዳላቸው ካረጋገጡ በኋላ፣ ለ16 ወራት እርቁን ለማምጣት ሲጥሩ ቆይተው፣ በመጨረሻ በሁለቱም በኩል ፍቃደኝነት መኖሩን ካረጋገጡ በኋላ የላኳቸውን ሽማግሌዎች ሰብስበው የደረሱበትን እንዳሳወቁ ተናግረዋል።

በሀገሪቱ ላይ ሠላም፣ እርቅና መረጋጋት እንዲመጣ፣ የማንኛውንም የሽምግልና ቡድኑን እንቅስቃሴ በቀናነት እንደሚያዩት የገለፁት፤ የኦፌዲን ሊቀመንበር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ እሳቸው ቅር የተሰኙት፣ በውጭ የሚገኙ የኦሮሞን ጉዳይ ይዘው የተነሱ ኃይሎችን ከመንግሥት ጋር ለማስታረቅ ሲነሱ፣ በሀገር ውስጥ ያሉትንና በሕጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን ለማወያየት ጥረት አለመደረጉ ነው።

አምባሣደር ብርሃኑ፣ ሽማግሌዎቹ የወከሏቸው ኦነግንና መንግሥትን እንዲያቀራርቡ እንጂ ፓርቲዎቹን እንዲያወያዩ ባለመሆኑ እነሱን የሚያነጋግሩበት ምንም አጀንዳ እንደሌላቸው ገልጸዋል።

ጉዳዩ አንድ ከሆነና እንዲመጣም የሚፈለገው መፍትሔ ሀገራዊ ጥቅም ከሆነ፤ በሁለት የሽምግልና ቡድን ማየቱ ባህላዊ የሆነውን የሽምግልና ጽንሰ ሃሳብ ትርጉም ያበላሸዋል ይላሉ እኚህ አመራር። ከዚያ ይልቅ በተጀመረው መስመር ገብቶና በጋራ ተጠናክሮ፣ በተለያየ አቅጣጫ የተከፋፈለውን የኦሮሞ ቡድን አንድ ሊያደርግ በሚቻልበት መንገድ በማመቻቸት ሁሉንም ወገን በአንድ ላይ ማስታረቅ እንደሚገባ ይመክራሉ።

## ሽምግልና ለሀገር

አቶ ታምሩ፤ የሽምግልና እንቅስቃሴ መሠረቱ ሀገራዊ ስሜትና ለሀገር ማሰብ ነው ይላሉ። በሀገር ውስጥ ሠላም እንዲሰፍን፣ መብት እንዲከበር ከማድረግ አንፃር ሊታይ እንደሚገባ ይመክራሉ። ለምሳሌ እንደ ደቡብ አፍሪካ ያሉ አንዳንድ ሀገሮች፣ እንደዚህ ባሉ ባህላዊ እሴቶቻቸውን በሕገ መንግሥታቸው ላይ ሳይቀር እውቅና ሰጥተው የሚንቀሳቀሱ አሉ። እኛ ሀገርም ይህ ባህል አለ። ለምሳሌ ዘመናዊ ሕጎች ከመውጣታቸው በፊት ሰው ይተዳደር የነበረው፣ በአካባቢው ባለ ባህላዊ አስተዳደርና አመራር ስለሆነ፣ ባልና ሚስት ሲጣሉ፣ ጎረቤት ከጎረቤት ጋር ሲጋጭ፣ የአካባቢ አለመግባባት ሲኖር፣ በዕድሜያቸው ጠና ያሉ ባህሉንና ሥርዓቱን የሚያውቁ ሰዎች ተሰባስበው ሁለቱንም ወገኖች በግል አነጋግረው፣ ከዛ ደግሞ በጋራ አቀራርበው ሲያስማሙና ሲያስታርቁ ይታያል። ሽማግሌዎቹ አደባባይ ወጥተው እንዲህ አድርገናል አይሉም የተጣሉ ሰዎች ሲታረቁ የተቀያየሙ ሰዎች ሲቀራረቡ ከዚህም አልፎ ግለሰቦች ብቻ ሳይሆን ማኅበረሰብም ጭምር ሲቀራረብ ይታያል። በዚህም የተነሳ ሽምግልና "ይታያል እንጂ አይሰማም"። ይኼ ባህላችን በየማኅበረሰቡ ማስታረቅ በፍርድ ከመገልገል እጅግ ይለያል። ፍርድ ማለት ሰይፍ ማለት ነው። የተረታው ተሸናፊ፣ የረታው ደግሞ አሸናፊ ይሆናል። ስለዚህ በቂምና በበቀል ተወጣጥረው እንዲኖሩ በር ይከፍታል። በእርቅ የሚያልቅ ከሆነ ግን አንተም ተው አንተም ተው፣ ይሆንና አሸናፊም ተሸናፊም አይኖርም።

"ሽምግልና በባህላችን የሚጣላ አይደለም፤ የኃይል፣ የጉልበት፣ የጭካኔና የመበቃቀል አካሄድ ቀርቶ፤ ተሸናፊና አሸናፊ የሌለበት፣ ሁሉም ደስተኛ ሆኖ፣ እርካታ አግኝቶ የሚወጣበት እርቅ ካለ በጣም ጥሩ ነው" ይላሉ አቶ ስዩ አብርሃ።

እስር ቤት በነበሩበት ጊዜ፤ ከእስር ቤቱ ግቢ ውስጥ ካሉት እስረኞች በርካታዎቹ የኦሮሞ ተወላጅ የነበሩ መሆናቸውን መመልከታቸውን ይገልፃሉ።

እነሱንና ሌሎች እስረኞች እንዲፈቱ ጥረት መደረጉ፣ እስረኞችን ማስፈታቱና፣ በተለያየ ምክንያት ከኢትዮጵያ ወጥተው መመለስ የማይችሉና በዱር በገደሉ ለትጥቅ ትግል የተሰለፉ ሰዎች ሠላምና፣ እርቅ ወርዶ ሀገራቸው እንዲገቡና፣ ከቤተሰቦቻቸው እንዲቀላቀሉ ለማድረግ ጥረት መጀመሩ የሚበረታታና የሚደገፍ ተግባር እንደሆነ አቶ ስዩ ይገልፃሉ።

በሀገራችን ሲዳከሙ የነበሩ ባህሎች እንዲፋፉና እንዲጠነከሩ፣ የነበራቸውን ክብርና ዝና እንዲያገኙ በሽምግልና መታየቱ በጎ ነገር ነበር። አሁን ያለው የሽምግልና ሂደት መቋጫው አሸናፊና ተሸናፊ የሌለበት፤ ሁሉም አሸናፊ ሆኖ የሚወጣበት የእውነት ይቅር ለእግዚአብሔር የሚያባብልና የእርቅ ሥርዓት ሊሆን እንደሚገባ ይመክራሉ።

አሁን ባሉት ሽማግሌዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚደረገውንም የሽምግልና ሂደት በትክክለኛው የእርቅ ሥርዓት የተከናወኑ ናቸው? ወይስ የኢህአዴግ የፖለቲካ መጠቀሚያ? የሚሉትን ጉዳዮችን እየነጣጠሉ በዝርዝር ማየት እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል።

በመገናኛ ብዙኀን ስለተሰማው ጉዳይ በተመለከተ፣ በአንድ በኩል ሽምግልና እየተባለ በአንድ በኩል ማሰር ሲታይ፤ ግልፅ የሆነ ነገር ለመናገር ይከብዳል።

የቆዩቱን እየፈቱ አዲሶቹን በዙር ማስገባት ከሆነ ደግሞ፤ ኢህአዴግ አንዳንድ ጊዜ፣ አንዳንድ ፖለቲከኞች አደገኛ ናቸው ሲላቸው ያስራቸዋል፣ አደገኛነታቸው እምብዛም አይደለም ሲል ደግሞ ይፈታና ሌሎችን በልዋጭ ያስራል።

"ጉዳዩ በሽምግልና ከተያዘ፤ አሸባሪ ነው፤ አነግ ነው፣ ተባባሪ ነው እያሉ ሰዎችን ማሰር ምን አመጣው? የሚል ነገር ያስነሳል፤ እርቅ የሚባለው ነገር እውነት የምር ነው? ከቅን ልቦና ከኢትዮጵያዊነት፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ከማቀራረብ በበጎ መንፈሥ የሚሠራ ዘላቂነት ያለው ነው ወይስ እንዲያው ለአጭር ጊዜ ለፕሮፓጋንዳ ተብሎ የሚሠራ ነው? የሚል ጥያቄ እንዳነሳ ያደርገኛል" ይላሉ አቶ ስዩ አብርሃ።

"የሀገር ሽማግሌዎች ሚና የላቀ ሊሆን የሚችለው የሀገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች የመቻቻል ፖለቲካ መከተል ሲፈልጉ ነው" የሚሉት ዶ/ር መረራ ጉዲና በኢትዮጵያ ጉልበቱም ሆነ ሀብቱ ያለው በኢትዮጵያ መንግሥት እጅ በመሆኑ፣ መንግሥት በሀገራዊ አጀንዳዎች ከተቃዋሚ የፓለቲካ ፓርቲዎችም ጋር በክብ ጠረጴዛ ለመወያየት ዝግጁነት ካላሳየ ችግር በተፈጠረ ቁጥር የሀገር ሽማግሌዎች እየገቡ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ጊዜያዊ ጨዋታ ነው" ይሉታል።

የሽማግሌ ቡድን መቋቋምም ሆነ መግባት፣ የሀገሪቱን የፖለቲካ ችግር ሊፈታው እንደማይችል ሁሉንም ወገኖች ያስማማል። መንግሥት የሽምግልና ጉባዔ ስብስቡን በተለያየ መንገድ እንዲቋቋም ግፊት እያደረገ፣ ለወቅታዊ የፖለቲካ ትኩሳት መወጣጫ የሚያውለው ከሆነና፣ አሸማጋዮቹም በቡድን እየተከፋፈሉ "ሽምግልና" የሚለውን ባህላዊ እሴት አላግባብ ከተጠቀሙበት ሽምግልናው ዋጋ እንደሚያጣም አስተያየት ሰጪዎቹ ይናገራሉ።